810 00 250/14
16/01/2011

753/2013

ለፌዴራል ከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ
**<u>አዲስ አበባ</u>**

ጉዳዩ፡ <u>የጸደቀ መመሪያ ስለመላክ</u>

ተጎጂ ከስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ መመሪያ ጸድቆ እንዲላክላችሁ በቁጥር 8/ስ-6-1/2011 መስከረም 11 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡ የዚህ መመሪያ ጠቅላላ ይዘት ሲመረመር ብዙ ባለድርሻ አካላትን የሚያሳትፍ መሆኑ ቢታወቅም በአስተባባሪነት እየመራ ያለው ኤጀንሲው በመሆኑና የማስተባበሩም ተግባር ኤጀንሲው ከተቋቋመበት ደንብ አኳያ ተመርምሮ አዘጋጅታችሁ የላካችሁልን መመሪያ ቁጥር 65/2011 ሆኖ ከመስከረም 15 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ተወስኗል፡፡

ስለዚህ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንድትከታተሉና እንድታስፈጽሙ የጸደቀውን 1 ጥራዝ መመሪያ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ጃንጥራር አባይ ይግዛው
ሚኒስትር

ግልባጭ፡-

- ለክብርት ሚኒስትር ዴኤታ ( የከተማ ልማት ዘርፍ)፣
- ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ ( የቤቶችና መሠረተ ልማት ዘርፍ)፣
- ለሚኒስትር ጽ/ቤትና ሚኒ ካቢኔጉዳዮች ቢሮ
- ለሕግ ዳይሬክቶሬት

**<u>ከ/ል/ቤ/ሚ</u>**

810 መ250/14
16/01/2011

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# በፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

# ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 753/2013

መስከረም 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ

## ማውጫ


መግቢያ፡- ..... 3
1. አጭር ርዕስ፡- ..... 4
2. ትርጓሜ፡- ..... 4
3. የተፈፃሚነት ወሰን፡- ..... 4
4. ዓላማ፡- ..... 4
5. መርሀ፡- ..... 5
6. የተጎጂ የስደት ተመላሽ መለያ መስፈርት ..... 5
7. ስለ ስደት ተመላሽ ምዝገባ ..... 6
8. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴ መቋቋም ..... 6
9. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት ..... 7
10. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴው አሠራር ..... 7
11. ስለሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች ..... 8
12. ስለተሃድሶ የድጋፍ ማዕቀፍ ..... 8
13. ስለ ማህበራዊ አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፍ ..... 8
14. ስለ ኢኮኖሚያዊ የድጋፍ ማዕቀፍ ..... 9
15. ስለድጋፍ አሰጣጥ እርከን ..... 9
16. እርከን አንድ ..... 9
17. እርከን ሁለት ..... 10
18. እርከን ሦስት ..... 10
19. እርከን አራት ..... 11
20. የድጋፍ ሽግግር ..... 11
21. ድጋፉ ስለሚቆይበት ጊዜ ..... 11
22. ስለድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጥምረት መደራጀት ..... 11
23. የጥምረቱ ተግባርና ኃላፊነት፡- ..... 13
24. በጥምረቱ የሚሳተፉ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት ..... 13
25. ስለድጋፉ የሀብት ምንጭ ..... 14
26. ሀገር አቀፍ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት ስለማደራጀት ..... 14
27. ስለ አገር አቀፍ የተጎጂ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት ይዘት ..... 14
28. ስደት ተመላሽ መረጃ አሰባሰብ ..... 15
29. ስለ አገር አቀፍ የተጎጂ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት አጠቃቀም ..... 15
30. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ..... 16
31. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት፣ ..... 16
32. በድጋፍ አሰጣጥ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ ..... 17
33. ስለተሻሩ መመሪያዎች ..... 17
34. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ ..... 17




* የሴቶችና ሕፃናት ጉዳዮች ሚኒስቴር * ... ማህበር ... ሪፐብሊክ

## መግቢያ፡-

በአገራችን በርካታ ወገኖቻችን በተለይም ሴቶች እና ወጣቶች በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ተለያዩ መዳረሻ አገራት በህጋዊና በህገ-ወጥ መንገድ ስለሚሰደዱ፤ በዚህም የተነሳ ለአካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ችግሮች እየተጋለጡ በመሆኑ፣

መንግስት የችግሩን ስፋት እና አሳሳቢነት በመረዳት የስደት ተጎጂው ድጋፍ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ የሚደነግግ የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የወጣ አዋጅ እና የኢትዮጵያ የውጭ አገር ሥራ ሥምሪት የወጣና ይህንንም ለማስፈፀም የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን የቀረፀ ቢሆንም የሚሰጠውን መልሶ የማቋቋም ድጋፍ እና የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓቱን አስመልክቶ የሚዘረዝር ደጋፊ መመሪያ ሳያወጣ የቆየ በመሆኑ፣

የአፈፃፀም መመሪያ ባለመኖሩ ምክንያት በተለያዩ ጊዜያት ወደ አገር ቤት የሚመለሰውን የስደት ተጎጂ ዜጋ መልሶ የማቋቋሙ ሂደት ሁሉንም በፍትሀዊነት፣ በተደራሽነት እና ወጥነት ባለው መልኩ ተጠቃሚ ማድረግ እንዳይቻል፣ የባለድርሻ አካላት ሚናና ተሳትፎ ግልጽነት የጎደለው እንዲሆን እንዲሁም የመረጃ አያያዝ ሥርዓቱም ጉድለት የነበረበት እንዲሆን አድርጎ የቆየ በመሆኑ፣

መመሪያው ሲዘጋጅ በግብርናና እንስሳት ሐብት ሚኒስቴር ስር የተደራጃው የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ ዘርፍ የተወከለ ባለሙያ፣ ከክልሎችና ከፌደራል የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ግንቦት 22 ቀን 2010 ዓ.ም ባደረጉት የጋራ መድረክ ላይ እንደሀገር በአንድ መመሪያ መመራት እንዳለበትና መመሪያውም በከተሞች ሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተዘጋጅቶ በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ጸድቆ እንዲወጣ መግባባት ላይ በመደረሱ፣

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/ 2008 አንቀጽ 7 ንኡስ አንቀጽ 8 እንዲሁም አንቀጽ 14 መሠርት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## 1. አጭር ርዕስ፡-

ይህ መመሪያ "ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዜጎችን መደገፊያና መልሶ ማቋቋሚያ መመሪያ ቁጥር 753/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. ትርጓሜ፡-

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1. "ተጎጂ ከስደት ተመላሽ" ማለት በማንኛውም ምክንያት በፍላጎቱም ይሁን ተገዶ በህጋዊም ይሁን በህገወጥ መንገድ ከአገሩ ወጥቶ በቆይታ ጊዜው ሳይወሰን፤ በጉዞ ላይም ይሁን በመዳረሻ አገራት ለተለያዩ ጥቃቶች ወይም የብዝበዛ አይነቶች ተጋልጦ አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነ-ልቦናዊ፣ ወይም ማህበራዊ ጉዳት ደርሶበት ወደ አገሩ የተመለሰ ወይም እንዲመለስ የተደረገ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነው።
2. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯(፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል።
3. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው አገላለጽ ሴትንም ይጨምራል።

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን፡-

1. ይህ መመሪያ በህጋዊም ሆነ በህገወጥ መንገድ ከአገሩ ወጥቶ በመተላለፊያም ሆነ በመዳረሻ አገራት ለተለያዩ ጉዳቶችና የብዝበዛ አይነቶች ተጋልጦ ወደ አገሩ በሚመለስ የኢትዮጵያ ዜጋ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣
2. መንግስታዊ እና መንግሰታዊ ባልሆኑ አካላት የሚሰጡ የተጎጂ ስደት ተመላሽ ድጋፎች በዚህ መመሪያ መሠረት ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

## 4. ዓላማ፡-

ለተጎጂ ከስደት ተመላሽ በተበታተነ እና በዘመቻ መልክ እየተሠጠ ያለውን መልሶ የማቋቋም ድጋፍ ወጥ፣ ተደራሽ እና ፍትሐዊ እንዲሆን ማስቻል ነው።



የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር

## 5. መርህ፡-

ለተጎጅ ከስደት ተመላሽ የሚሰጠው ድጋፍና አገልግሎት የሚከተሉትን መርሆዎች ከግምት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል፡፡

1. ፍቃደኝነትን መሠረት ያደረገ፣
2. የህፃናትን፣ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎት መሠረት ያደረገና ቅድሚያ የሚሰጠ፣
3. ሰብዓአዊ መብቶችን ማክበር፣
4. ከማንኛውም አድሎና መገለል ነፃ የሆነ፣
5. አሳታፊነት፣
6. ማህበረሰብ አቀፍ፣
7. ፍትሃዊነት፣
8. ልዩ ባህሪና ፍላጎትን መሠረት ያደረገ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ፣
9. ምስጥርን መጠበቅ፣
10. ጥገኝነት የማያበረታታ ድጋፍ፡፡

## 6. የተጎጂ የስደት ተመላሽ መለያ መስፈርት

ማንኛውም አመልካች ተጎጅ የስደት ተመላሽ ሆኖ የሚለየው፡-

1. አመልካቹ፡-
   ሀ) በሚመዘገብበት የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ነዋሪ የነበረ ወይም ነዋሪ ስለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል እና፣
   ለ) የስደት ተመላሽ ስለመሆኑ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ መንግስታዊ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ሌሎች አግባብነት ካላቸው ተቋማት ህጋዊ ማሥረጃ ማቅረብ የሚችል፣
   ሐ) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ 'ለ' ላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረብ የማይችል አመልካች የስደት ተመላሽ ስለመሆኑ ከሚኖርበት ቀበሌ ወይም ወረዳ አስተዳደር የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣
   መ) በቤተሰብ አስተዳደር ሥር ያለ ህፃን ወይም የአዕምሮ ህመምተኛ ከሆነ በአሳዳሪው ወይም በሞግዚቱ አማካይነት በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ 'ለ' ላይ የተጠቀሰውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፣

2. የስደት ተመላሽ ሆኖ ከወላጅ ወይም ከቤተሰብ የተነጠለ ወይም ወላጆቹን ያጣ ህፃን መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ፣

3. የስደት ተመላሹ በሚመለከተው የህግ አስፈጻሚ አካል መደበኛ የሥራ ሂደት በህገወጥ የሰዎች ዝውውር ወንጀል ምክንያት ለተለያዩ የብዝበዛ አይነቶች ስለመጋለጡ ማስረጃ ያቀረበ ከሆነ ነው፡፡

## 7. ስለ ስደት ተመላሽ ምዝገባ

በዚህ መመሪያ መሠረት ድጋፍ እንዲደረግለት የሚፈልግ ከስደት ተመላሽ ምዝገባ፡-

1. በማንኛውም የሥራ ቀናት በከተሞች ወይም በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ወይም በገጠር ቀበሌ ባሉ ባለሙያዎች ይከናወናል፡፡

2. ምዝገባውን የሚያከናውነው ባለሙያ አመልካቹ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1 እስከ 3 የተጠቀሱት ሁኔታዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ ምዝገባውን ያከናውናል፡፡

## 8. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴ መቋቋም

1. ለወረዳ ወይም ለከተማ የድጋፍ ሰጭ አካላት ጥምረት ተጠሪ ሆኖ በከተማ ወይም በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽሕፈት ቤት አስተባባሪነት የሚመራ ተጎጂ የስደት ተመላሾች ልየታ የቴክኒክ ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ የቴክኒክ ኮሚቴ እየተባላ የሚጠራ) በዚህ መመሪያ ተቋቁሟል፡፡

2. የቴክኒክ ኮሚቴው አባላት፡-

   የቴክኒክ ኮሚቴው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

   ሀ. የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ሰብሳቢ

   ለ. የከተማ/ወረዳ የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ------ ም/ሰብሳቢ

   ሐ. የከተማ/የወረዳ ወጣቶችና ስፖርት ጽ/ቤት -------------------- ፀሐፊ

   መ. የከተማ/የወረዳ ጤና ጽ/ቤት ------------------------------------ አባል

   ሠ. የከተማ/ወረዳ የሴቶችና የህጻናት ጽ/ቤት -------------------- አባል

   ረ. የከተማ የህዝብ አደረጃጀትና ተሳትፎ አማካሪ -------------------- አባል

   ሰ. የከተማ ነዋሪዎች ፎረም ሰብሳቢ ------------------------------ አባል



የኢትዮጵያ ... ማህበር የሥራ ሄደት

## 9. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት

ኮሚቴው፡-

1. በከተማ ወይም በገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት አንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ወይም በገጠር ቀበሌ የተመዘገበ አመልካች ትክክለኛ ተጎጂ የስደት ተመላሽ ስለመሆኑ በምዝገባ ወቅት በቀረበ ማስረጃ፣ አመልካቹን ቃለ-መጠይቅ በማድረግ እና እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ የተጎጅነት መለያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃዎችን በመሰብሰብ ያረጋግጣል፣
2. የቴክኒክ ኮሚቴው ዝርዝር የውሳኔ መረጃውን ተመዝጋቢዎች ምዝገባወን ባከናወኑበት ማዕከል ወይም የገጠር ቀበሌ ግልጽ በሆነ ቦታ በመለጠፍ ያሳውቃል፣
3. አመልካቹ ተጎጂ የስደት ተመላሽ መሆኑን ሲያረጋግጥ ያለበትን ሁኔታና የሚያስፈልጉትን የድጋፍ አይነቶች በመለየት ተጎጂውን ከውሳኔ ማስረጃው ጋር አገልግሎት ወደ ሚያገኝበት አካል ይልካል፣
4. ተጎጂ የስደት ተመላሹ በተሰጠው ውሳኔ መሠረት ከሚመለከተው ተቋም ማግኘት የሚገባውን አገልግሎት እያገኘ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፣
5. ተጎጂ ስደት ተመለሻ በቀጣይ ሊሰማራበት የሚፈልገውን የሥራ ዘርፍ ለይቶ ይመዘግባል፣
6. የተለየውን ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዝርዝር መረጃ እና እንዲደረግለት የተወሰነውን የድጋፍ ዓይነት በማጠናቀር መረጃውን ለከተማው ወይም ለገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ጽሕፈት ቤት ይልካል።

## 10. ስለ ቴክኒክ ኮሚቴው አሠራር

**የቴክኒክ ኮሚቴው፡-**

1. በሳምንት አንድ ቀን ይሰበሰባል፣ እንደ አስፈላጊነቱ መደበኛ ያልሆነ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፣
2. ከኮሚቴው አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኘ ምልአተ ጉባዔ ይሆናል፣
3. የኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ የሚወሰን ሆኖ ድምፅ እኩል ለኩል በሚከፈልበት ሁኔታ ሰብሳቢው የተስማማበት ሃሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፣
4. በኮሚቴው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ወይም ተጎጂ የስደት ተመላሽ ቅሬታውን በአንቀጽ 31 በተቀመጠው የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት ሊያቀርብ ይችላል።

## 11. ስለሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች

1. ተጎጂ የስደት ተመላሽ መሆኑ ለተረጋገጠ ሰው የሚሰጥ የመልሶ ማቋቋም የድጋፍ ማዕቀፍ በተለያየ ዘርፍ የሚከናወን ሆኖ የተጎጂውን ልዩ ፍላጎት፣ ነባራዊ ሁኔታ እና ያለውን ድጋፍ የመስጠት አቅም ያገናዘበ ይሆናል፤
2. ለተጎጂ የስደት ተመላሽ የሚሰጥ የድጋፍ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡
   ሀ. የተሃድሶ የድጋፍ ማዕቀፍ፣
   ለ. የማህበራዊ አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፍ፣
   ሐ. ኢኮኖሚያዊ የድጋፍ ማዕቀፍ፡፡

## 12. ስለተሃድሶ የድጋፍ ማዕቀፍ

ለተጎጂ የስደት ተመላሽ በተሀድሶ የሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1. ጊዜያዊ የመጠለያ ድጋፍ (ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዜጎች እንደየጉዳታቸው መጠን እየታዩ ከቤተሰቦቻቸው ወይም ወደመጡበት አካባቢ እስኪመለሱ ድረስ ጊዜያዊ መጠለያ ድጋፍ የሚያገኙበት)፣
2. የጤና ምርመራ እና የህክምና ድጋፍ አገልግሎት፣
3. የሥነ-ልቦና ምክር አገልግሎት፣
4. አልባሳት እና የምግብ አገልግሎት ድጋፍ፣
5. መሠረታዊ የቤት ውስጥ መገልገያ መሣሪያዎች ድጋፍ፣
6. የትራንስፖርት ድጋፍ አገልግሎት፣
7. አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫና የህይወት ክህሎት ሥልጠና፡፡

## 13. ስለ ማህበራዊ አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፍ

ለተጎጂ የስደት ተመላሽ በማህበራዊ አገልግሎት የሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1. ከቤተሰብ ጋር መልሶ ማቀላቀል፣
2. ነፃ የፍትህ አገልግሎት ድጋፍ፣
3. የማህበራዊ ተግባቦት ድጋፍ፣ወይም
4. የትምህርት እና መርጃ መሣሪያዎች ድጋፍ፣



የሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

## 14. ስለ ኢኮኖሚያዊ የድጋፍ ማዕቀፍ

ለተጎጂ የስደት ተመላሽ በኢኮኖሚያዊ አገልግሎት የሚደረግ የድጋፍ ማዕቀፍ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1. የሥልጠና፣ የማማከር ወይም የሥራ ዕድል ፈጠራ አገልግሎት ድጋፍ፡-
   ሀ) በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የቅጥር አገልግሎት ድጋፍ፣
   ለ) አጫጭር የቴክኒክ እና የሙያ ትምህርት ሥልጠና፣
   ሐ) የንግድ ልማት ሥልጠና እና ዕቅድ ዝግጅት ድጋፍ፣
   መ) የማደራጀት እና ህጋዊ ሰውነት የማስጠት ድጋፍ፣
   ሠ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት፣ወይም
   ረ) ሌላ አስፈላጊ የቴክኒክ ክህሎት ሥልጠና ድጋፍ፡፡
2. የመነሻ ካፒታል አቅርቦት ድጋፍ፡-
   ሀ) የገንዘብ ቁጠባና ብድር አቅርቦት፣
   ለ) በቀጥታ የሚሰጥ የተዘዋዋሪ የገንዘብ አቅርቦት፣
   ሐ) የመሣሪያ ሊዝ አቅርቦት፣
3. የመሥሪያና መሸጫ ቦታ አቅርቦት ድጋፍ፡፡
4. የገበያ ትሥሥር ድጋፍ፡፡

## 15. ስለድጋፍ አሰጣጥ እርከን

ለተጎጂ የስደት ተመለሽ የሚሰጥ የድጋፍ ማዕቀፍ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 መሠረት የተገለጹ የድጋፍ ዘርፎችን የሚያቅፍ ሆኖ የተጎጂ የስደት ተመላሽ ልዩ ፍላጎትና በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 16 እስከ 19 የተመለከቱትን የድጋፍ አሰጣጥ እርከኖች ታሳቢ በማድረግ ይፈፀማል፡፡

## 16. እርከን አንድ

በእርከን አንድ ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከስደት ተመላሹ ወደ መኖሪያ አካባቢው ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አንድ ወር የሚደረግ የድጋፍ አገልግሎት ሲሆኑ እንደ አስፈላጊነቱ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1. ስለሚያገኙት ድጋፍ እና የድጋፍ አሰጣጥ ላይ ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
2. አልባሳት እና የምግብ አገልግሎት ድጋፍ፣
3. የምግብ ማብሰያ መሣሪያዎች፣ ፍራሽ እና ብርድልብስ ድጋፍ፣



የሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

4. ጊዜያዊ መጠለያ፣
5. የጤና ምርመራና የሕክምና አገልግሎት፣
6. የሥነ ልቦና ምክር አገልግሎት፣
7. ከቤተሰብ ጋር መልሶ ማገናኘት እና ማቀላቀል፣
8. የትራንስፖርት አገልግሎት ድጋፍ፣
9. የሕግ ድጋፍ አገልገሎት።

## 17. እርከን ሁለት

በእርከን ሁለት ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከስደት ተመላሹ ወደ መኖሪያ አካባቢው ከደረሰ በኋላ ከአንድ እስከ ሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ የሚደረግ የድጋፍ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

1. የትምህርት እና መርጃ መሣሪያዎች ድጋፍ፣
2. የህይወት ክህሎት እና አስተሳሰብ ለውጥ ሥልጠና፣
3. የማህበራዊ ተግባቦት ግንዛቤ ድጋፍ፣
4. ተጎጂ የስደት ተመላሽ የሆነ ከወላጅ ወይም ቤተሰብ የተነጠለ እና ወላጅ ያጣ ህፃን አማራጭ ድጋፍ እና እንክብካቤ አገልግሎት፣
5. በመሠረታዊ የንግድ ሃሳብ፣ ሥራ ፈጠራ እና ዕቅድ ዝግጅት ክህሎት ሥልጠና፣
6. ተጎጂ የስደት ተመላሹን ፍላጎት መሠረት ያደረገ አጫጭር የቴክኒክ እና የሙያ ሥልጠና አገልግሎት ወይም፣
7. በጊዜያዊ ወይም በቋሚ የቅጥር አገልግሎት ድጋፍ።

## 18. እርከን ሦስት

በእርከን ሦስት ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከስደት ተመላሹ ወደ መደበኛ መኖሪያ አካባቢው ከተመለሰ ከሦስት ወራት ጊዜ ጀምሮ የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል።

1. ሊሠማራበት በፈለገው የሥራ መስክ የሚያስፈለግ በቂ የሙያ ክህሎት ሥልጠና፣
2. የማደራጀት እና ህጋዊ ሰውነት የማሰጠት ድጋፍ፣
3. የመሥሪያ እና መሸጫ የሚሆን ቦታ ለሚፈልግ ቦታውን እንዲያገኝ መደገፍ፣



የሰራተኛ ና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

4. ለሥራ መነሻ የሚሆን ገንዘብ ለሚያስፈልገው ከመደበኛ ብድር ወይም ተዘዋዋሪ ፈንድ ድጋፍ፣
5. የመሣሪያ ሊዝ አቅርቦት፣
6. የገበያ ትሥሥር አገልግሎት፣
7. የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ወይም
8. የሽግግር ድጋፍ ማዕቀፍ አገልግሎት፡፡

## 19. እርከን አራት

በእርከን አራት ሥር የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ተጎጂ ከስደት ተመላሹ በዘላቂነት እና በተረጋጋ መልኩ ህይወቱን እንዲመራ ለማስቻል የሚሰጥ የድጋፍ አገልግሎት ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

1. በተሠማራበት የሥራ ዘርፍ የማብቃት ድጋፍ አገልግሎት ወይም
2. የክትትል፣ የምክር እና ቴክኒካዊ ድጋፍ አገልግሎት፡፡

## 20. የድጋፍ ሽግግር

1. በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 16 እስከ 19 ባሉ እርከኖች የሚሰጡ ድጋፎች በእርከኑ የትግበራ ጊዜ ውስጥ ካልተጠናቁ እና የድጋፉ መቀጠል አስፈላጊ መሆኑ ድጋፉን እያደረገ ባለው ተቋም ሲታመንበት እየተሰጠ ያለው ድጋፍ በቀጣዩ የእርከን ጊዜ ውስጥ ቀጥሎ የሚፈፀም ይሆናል፡፡
2. ከእርከን አንድ እስከ አራት የሚሰጡ የድጋፍ ማዕቀፎች እንደ አስፈላጊነቱ በቅደም ተከተል ወይም የእርከን ጊዜ ቆይታውን ሳይጠበቅ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

## 21. ድጋፉ ስለሚቆይበት ጊዜ

በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 18 እርከን ሦስት እና በአንቀጽ 19 እርከን አራት ሥር የተዘረዘሩት የድጋፍ ማዕቀፎች የመተግበሪያ ጊዜ ቆይታ በመደበኛው የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና አሠራር ሥርዓት የሚመራ ይሆናል፡፡

## 22. ስለድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጥምረት መደራጀት

1. በክልል፣ ዞን፣ ክ/ከተማ፣ በወረዳ ወይም በከተማ የድጋፍ ሰጭ አካላት ጥምረት ስለመደራጀቱ:-



የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና

በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር እና ስደተኞችን በሕገ ወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀልን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 909/2007 አንቀጽ 40 መሠረት በፌዴራል ደረጃ የተቋቋመው ግብረ-ኃይል የተጎጂዎች ድጋፍ ቡድን እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ. የተጎጂዎች ድጋፍ ሰጪ ተቋማት ጥምረት በክልል፣ በዞን ወይም ክፍለ ከተማ እና በወረዳ ወይም በከተማ ደረጃ ይደራጃል፣

ለ. በየደረጃው የሚገኙት የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ ዳይሬክተር ወይም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የጥምረቱ ሰብሳቢና ጸሐፊ በመሆን ያስተባብራል፣

2. የጥምረቱን ሥራ የሚያስተባብር የባለሙያዎች ቡድን በከተማ ወይም ገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ጽህፈት ቤት ሥር ይዋቀራል፡፡

3. በየደረጃው የሚዋቀረው ጥምረት ከሚከተሉት ተቋማትና የሥራ ኃላፊዎች ይወከላል፡፡

ሀ. የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ (ሰብሳቢ)፣

ለ. የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ተወካይ ኃላፊ (ምክትል ሰብሳቢ)፣

ሐ. የሴቶችና ህፃናት ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

መ. የወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

ሠ. የትምህርት ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

ረ. የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ወይም ተቋም ምክትል ዳይሬክተር፣

ሰ. የአነስተኛ ብድርና ቁጠባ ተቋማት ምክትል ዳይሬክተር፣

ሸ. የጤና ጥበቃ ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

ቀ. የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

በ. የፍትህ ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ፣

ተ. የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ትብብር ቢሮ ወይም ጽሕፈት ቤት ምክትል ኃላፊ እና

ቸ. ሌሎች ድጋፍ አድራጊ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶች ተወካይ (ኃላፊ)፡፡

## 23. የጥምረቱ ተግባርና ኃላፊነት፡-

ጥምረቱ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡፡

1. የጥምረቱን ዓመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር በጋራ ያዘጋጃል፣
2. በጥምረቱ የተዘጋጀውን ዓመታዊ የድርጊት መርሃ-ግብር የሥራ አፈፃፀም በየ 3 ወሩ እየተገናኘ ይገመግማል፤ የተስተዋሉ ክፍተቶች ሲገኙ የመፍትሔ ሀሳብ ያስቀምጣል፣
3. በዓመት አንድ ጊዜ ከተጎጂ የስደት ተመላሾች ጋር የሚገናኝበት የውይይት መድረክ ያመቻቻል፣
4. እንደአስፈላጊነቱ ተጎጂ ተመላሾች ስላሉበት ሁኔታ ለማረጋገጥ ወይም ለመከታተል የመስክ ጉብኝት ያደርጋል፣
5. በአንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 የተጠቀሱት የጥምረቱ ትግባራትና ኃላፊነቶች እንደተጠበቁ ሆነው የጥምረቱ አባል ተቋማት ከተጎጂ ስደት ተመላሾች ፍላጎት እና ከተቋቋሙበት ዓላማና ተልዕኮ አንጻር ታሳቢ አድርገው ይተገብራሉ፡፡

## 24. በጥምረቱ የሚሳተፉ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት

በጥምረቱ ተሳታፊ የሆኑ ተቋማት የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት አለባቸው፡-

1. በሚዘጋጀው ዓመታዊ የድርጊት መርሀ-ግብር መሠረት እና የቴክኒክ ኮሚቴው በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሠረት ውሳኔውን በማጸደቅና በማስተላለፍ ከተቋማቸው የሚጠበቀውን ድጋፍ ይሰጣሉ፣
2. የሚሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የተጎጂ ስደት ተመላሽ ጉዳይ የሚከታተል አግባብነት ያለው ባለሙያ በየተቋማቸው ይመድባሉ፣
3. ለተጎጂው የሚሰጡ ክፍያ የሚጠይቁ አገልግሎቶች ወጪ የሚሸፈንበትን መንገድ ያመቻቻሉ፣
4. ለተጎጂው የሰጡትን ድጋፍና አገልግሎት አስመልክቶ ዝርዝር መረጃ በየደረጃው ለሚገኙ የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ወይም ጽ/ቤት በየወሩ ይልካል፣



* የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር * ... ማህደር የሥራ ሂደት

## 25. ስለድጋፉ የሀብት ምንጭ

ለስደት ተጎጂ የሚደረገው ድጋፍ የሚያስፈለገው በጀት፡-

1. ድጋፍ የሚሰጡ ተቋማት ድጋፉን ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን በጀት በዋናነት በተቋማቸው መደበኛ በጀት ይሸፈናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጎጂዎች ድጋፍ የሚሆን ሀብት ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት የማፈላለግ ሥራ የፌዴራሉና የክልል የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ደጋፊ አካላት ጋር በመቀናጀት ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

## 26. ሀገር አቀፍ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት ስለማደራጀት

በየጊዜው ወደ አገራቸው የሚመለሱ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ዝርዝር መረጃ የሚያዝበት ሀገር አቀፍ የተመላሾች መረጃ ቋት በፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጅንሲ የመረጃ ክፍል ሥር ይደራጃል፡፡

## 27. ስለ አገር አቀፍ የተጎጂ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት ይዘት

በአገር አቀፍ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት ውስጥ የሚመዘገበው መረጃ የሚከተሉትን ዝርዝር የስደት ተመላሽ መረጃ መያዝ አለበት፡፡

1. ሙሉ ስም፣ ፆታ፣ ዕድሜ፣ የትውልድ ቦታ፣
2. የነበረበት አገር፣
3. ከአገር የወጣበት ሁኔታ፣ በህጋዊ መንገድ ከሆነ የላከው ኤጀንሲ ሥምና አድራሻ ወይም በህገወጥ ከሆነ የወጣበትን የመውጫ መስመር/በር፣
4. ከአገር ወጥቶ የነበረበትን ቀንና ዓመተ ምህረት፣
5. ወደ አገሩ የተመለሰበት ቀንና ዓመተ ምህረት፣
6. ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ የሄደበት ክልል፣ ዞንና ወረዳ፣
7. የተመላሹ ፎቶግራፍ፣
8. የደረሰበት የጉዳት አይነት፣
9. መረጃው በተወሰደበት ወቅት የስደት ተጎጂው የሚገኝበት ሁኔታ፣
10. ተመላሹ ድጋፍ ያገኘ ወይም ያላገኘ ስለመሆኑ፣
11. ድጋፍ ካገኘ ድጋፉን ያደረገለት አካልና የተደረገለት የድጋፍ አይነት፡፡

## 28. የስደት ተመላሽ መረጃ አሰባሰብ

1. የስደት ተመላሽ መረጃ አሰባሰብ ሂደቱ በተመላሹ ነጻ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ይሆናል።
2. የፌደራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ፦
   ሀ). በየጊዜው ወደ አገር የሚመለስ የስደት ተመለሽ ዝርዝር መረጃ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት በተለይም ከዓለም አቀፉ የፍልሰት ድርጅት (IOM)፣ ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ኤርፖርቶች ድርጅት፣ ከየዜግነትና ኢሚግሬሽን ጉዳይ መምሪያ ወይም ሌሎች አግባብነት ካላቸው ድርጅቶች ይሰበስባል።
   ለ). ተጎጂ ከስደት ተመላሽ ያገኘውን የድጋፍ አይነትና ድጋፍ ስላደረገው ተቋም የሚሰበሰበውን መረጃ አስመልክቶ ኤጀንሲው የሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ ያዘጋጃል፤ ለክልል ወይም ለከተማ መስተዳድር የከተማ እና የገጠር የሥራ እድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ ይልካል፣ በተዘጋጀው ቅጽ መሠረት መረጃውን በሦስት ወሩ ይቀበላል።
   ሐ). ከክልል ወይም ከከተማ መስተደዳደር የከተማ እና የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራ እና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ የተቀበለውን መረጃ በየስድስት ወሩ እየሰበሰበ ወደ አገር አቀፉ የተጎጂ የስደት ተመላሽ መረጃ ቋት ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል።

## 29. ስለ አገር አቀፍ የተጎጂ የስደት ተመላሾች የመረጃ ቋት አጠቃቀም

1. አገር አቀፉ የተጎጂ የስደት ተመላሽ የመረጃ ቋት አጠቃቀም በተቻለ መጠን የተጎጂ የስደት ተመላሽ የግለሰብአዊ መብት በማይነካና ምስጢራዊነቱ በተጠበቀ መንገድ መሆን አለበት፣
2. የተሰበሰበውን መረጃና የሚደራጀውን የመረጃ ቋት በየደረጃው በሚደራጁት የተጎጂዎች ድጋፍ ጥምረቶች የሚሳተፉና ድጋፍ የሚያደርጉ አካላት በቀላሉ ማግኘት እንዲችሉ የመረጃ ቋቱን ቁልፍ ወይም የይለፍ ምስጢራዊ ቁጥር እንዲያውቁት ይደረጋል።

## 30. የክትትልና ግምገማ ሥርዓት

ለተጎጂ የስደት ተመላሾች የሚደረገው አጠቃላይ የመልሶ ማቋቋምና ድጋፍ ተግባር በሚከተለው የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይመራል፡፡

1. በወረዳ ወይም በከተማ ደረጃ የሚገኝ ድጋፍ ሰጪ ተቋም ስለሰጠው የድጋፍ አይነት በየወሩ ለወረዳው ወይም ለከተማው የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡
2. የወረዳው ወይም የከተማው የከተማ ወይም የገጠር የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ጽሕፈት ቤት ከየተቋማቱ የተቀበለውን ሪፖርት በማጠናቀር በየሦስት ወሩ ለጥምረቱ በማቅረብ ግምገማ ያካሂዳል፤ በመደበኛነትም ለዞኑ ወይም ለክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. የዞን ወይም የክፍለ ከተማው ጽሕፈት ቤት ከየወረዳው ወይም ከየከተማው የተቀበለውን ሪፖርት በማጠናቀር በየሦስት ወሩ ለዞኑ ወይም ለክፍለ ከተማው ጥምረት በማቅረብ ግምገማ ያካሂዳል፤ በመደበኛነትም ለክልሉ ወይም ለከተማ አስተዳደር የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
4. የክልሉ ወይም ከተማ መስተዳደር የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ የተላከለትን ሪፖርት በማጠናቀር በየሶስት ወሩ በክልሉ ጥምረት ካስገመገመ በኂላ ለፌደራሉ የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ሪፖርት ይልካል፡፡
5. የፌዴራል የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ከየክልሉ ወይም ከየከተማ መስተዳደር የከተሞች የሥራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ የተቀበለውን ሪፖርት በማጠናቀር ለፌዴራል የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ግብረኃይል የተጎጂዎች ድጋፍ ቡድን ካስገመገመ በኂላ ለፌደራል የሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ተከላካይ ግብረ ኃይል ሴክሬታሪያት ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፡፡

## 31. ስለ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት፣

1. ማንኛውም አመልካች በቴክኒክ ኮሚቴው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ኮሚቴው ውሳኔውን በሰጠ በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ የውሳኔ ግልባጭ ይሰጠኝ አቤቱታ ማቅረብ ይኖርበታል፣



የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
ስርጭና ግሀደር የሥራ ሂደት

2. የቴክኒክ ኮሚቴው የሰጠውን የውሳኔ ቅጂ ቅሬታ አቅራቢው ጥያቄውን ካቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 3 የሥራ ቀናት ውስጥ መስጠት ይኖርበታል፣
3. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 10 መሠረት ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ቅሬታ አቅራቢ የኮሚቴውን ውሳኔና ሌሎች አስፈላጊ ማስረጃዎች በማያያዝ የውሳኔ ግልባጩ በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ ለወረዳው ወይም ለከተማው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ያቀርባል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት አቤቱታ የቀረበለት የወረዳው ወይም የከተማው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት አመልካቹ ያቀረበውን አቤቱታና የቀረበለትን ማስረጃ ከሕግ ጋር በማገናዘብ አቤቱታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት አስር የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፣
5. በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል በተለመደው በወረዳው ወይም በከተማው አስተዳደር ጽሕፈት ቤት የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል።

## 32. በድጋፍ አሰጣጥ ላይ ስለሚቀርብ ቅሬታ፡-

በድጋፍ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ድጋፉን በሚሰጠው አካል የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት መሠረት ይስተናገዳል።

## 33. ስለተሻሩ መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች የተጎጂ ከስደት ተመላሽ ዜጎችን መደገፊያና መልሶ ማቋቋሚያ መመሪያዎች፣ ሰርኩላሮችና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተሽረዋል።

## 34. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከመስከረም 15 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

ዶ/ንጋቱ ዳኛቸው?

ዳንጋቸው? አባይ

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚንስትር